## 2. አስተዳደር በሽግግር ዘመን

### 2. 1. ስፔን
በአቶ ኘሳ ኔስ

በስፔን የሽግግር ዘመን ከቀድሞው መንግሥት ሰዎች አንድ ፖሊስ እንኳን ከሥራ አልተባረረም:: ዳኞችም አስተዳዳሪዎቹም እንዳሉ ነው የቀጠሉት::ለውጥ የተደረገው የመንግ ተን ማእከላዊነት /ሴንትራላይዜሽን/ በሚያጠብቀው መዋቅርና የፖለቲካ ፖሊሲን በሚመለከት አንጻር ብቻ ነበር:: የአስተዳደር ሥራ የሚካሄድበትን ተቋም ቀየር ነው ዲሞክራሲያዊ ተቋም ተመሠረተ መንግሥትም በዚህ ዲሞክራሲያዊ አሠራር ዋስትና የመስጠት ሃላፊነት ወደቀበት::

ማእከላዊነትን /ሴንትራላይዜሽንን/ ከሚያጠብቅ አስተዳደር ወደ አውቶኖሚ ተሸጋገረን ቀደም ብዬ እንዳለኩት የብሄሮች ችግር የርስ በርስ ጦርነትን ከቀሰቀሱት ምክንያቶች አንዱ ነበር:: ይህንን ችግር በመፍታት በሃገሪቱ በሙሉ ሪጅናል አውቶኖሚ እንዲስፍን አደረገን:: የሀገሪቱን የአስተዳደር ካርታ ሙሉ በሙሉ ቀየር ነው:: 17 አቶኖመስ አስተዳደሮች ተመሠረቱ:: በዚሁ ለክ ፖርላሜንቶቹ፣መንግሥታት፣ የፍርድ ቤት አስተዳደሮች ተቋቋሙ::

የባስከን አገር ጋሊስን፣ ካታሎናንና አንዳሉዚያን በሚመለከት የተለየ ተጨማሪ ርምጃዎች ተወሰዱ:: ለእነዚህ አካባቢዎች ለሌሎች ከታወቀው አውቶኖሚ የሰፋ መብት ተሰጠ:: በዚህ ሁኔታ ጥያቄ ውስጥ የገባውና የፈረሰው ነባሩ የካስቲላኖች ሥርዐት ነው ማለት ይቻላል::

በሽግግሩ ዘመን አንድ ሚሊዮን የሚሆኑ የባርሴሎና ከተማ ነዋሪዎች ሰላማዊ ሰልፍ አድርገው የጠየቁት ዳቦ ሳይሆን ነጻነትና ራሳቸውን ለማስተዳደር የሚችሉበት ሁኔታ እንዲፈጠር ነበር:: በቀድሞው ሥርዓት የመንግሥት በጀት መቶ በመቶ ወደመእከሉ ነበር የሚሄደው አሁን ግን የተሻለና ዲሞክራሲያዊ ክፍፍል ተደረገ:: መእከላዊው መንግሥት 50% አቶኖመስ ሪጅኖች 25% ቀሪው 25% ደግሞ በወረዳዎች አስተዳደር እንዲገባ ተደረገ::

### 2. የቺሊ ሽግግር
በአቶ ለዊ ሚያራ

በቺሊ አዲስ የተቋቋመው የኘሬዚዳንት አይለዊን መንግሥት ከሁሉም በላይ የመከረው ከሠራዊቱ ጋር ፊት ለፊት ሳለመጋፈጥና ሳለመጋጨት ነበር:: እንዲያውም በአጠቃላዩ የተከለለው ፖሊሲ የፒኖሼን መንግሥት ይደገፈ የነበረትን የተለያዩ ክፍሎችጉዳይ ብቻ ለብቻ እያጠና መፍትሔ መሻት ነበር::

አሠሪዎችን በሚመለከት ቀደም ሲል የነበረውን የኢኮኖሚ ፖሊሲ ባለመቀየር መግባባት ተቻለ:: የቀኙ ፖርቲዎችን በሚመለከት በፖርላማ ካሉት ሁለት የቀኙ ፖርቲዎች ጋር ብቻ ለብቻ ውይይት ይካሄዳሉ:: ሠራዊቱን በሚመለከት ፒኖሼ ለኘሬዚዳንቱ ታዛዥ ሆነው የጦሩ የበላይ አዛዥነቱን እንደያዙ ቀጠሉ::

አስተዳደርን በሚመለከት የዲሴንትራላይዜሽን ሂደት ተጀምሯል:: የአካባቢና የገጠር አካባቢዎች አስተዳደር ዲሞክራሲያዊ እንዲሆንም ጥረት እየተካሄደ ነው:: በዚህ ላይ ደግሞ በህዝቡ በራሱ አነሳሽነት ለሚቋቋሙ የተለያዩ ማህበራት ድጋፍ የመስጠት ፖሊሲ አለ:: እንደቀድሞው መንግሥት በሞኖፖል በያዟቸው የመገናኛ ዘዴዎች በመጠቀም ከፋፋይ ኘሮፖጋንዳ

አያስፋፋም:: እንዲያውም ዛሬ መንግሥት ሆን ብሎ የያዘው ፖሊሲ የመቻቻል ልምድ በሀብረተሰቡ ሥር እንዲሰድ ምሳሌ የመሆን ፖሊሲ ሆኖ ይታያል:: የተከፋፈለች አገር አንዱ ጠላት ሌላው ወዳጅ እየተባለ የሚቧጨቀባት አገር በቅቶናል:: ዛሬ በሃገሪቱ የብሄራዊ እርቁ ሂደት በፍጥነት ሥር እንዲሰድ ሙከራ እየተደረገ ነው:: በዚህ ሳቢያም ዲሞክራሲ እየሰፋና እየተጠናከረ ይሄዳል ብለን እናምናለን::

### 3. ፖላንድ፣ በህዝቡ የተመረጡ መሪዎችና የቀድሞው አስተዳደር፣

አቶ ክራስናውለስኪ–ከፖላንድ ሳይንስ አካዳሚ
ዋርሶው ፖላንድ

በ1989 ዓ.ም. በተደረገው ምርጫ ሶሊደሪቲ ቢያሸንፍም አዲሱ መንግሥት ሲቋቋም የመከላከያንና የአገር አስተዳደር የመሳሰሉትን ቁልፍ ሚኒስትሮች ለኮሚኒስቶች መልቀቅ ተገደ ነበር:: ከፖርላሜንት አባላት አብዛኛዎቹ /የኮሚኒስት ፖርቲ አባላትም/ ለለውጥ የቆሙ ነበሩ::

በነዚህ የመጀመሪያዎቹ ምርጫዎች የህዝቡ ተሳትፎ 95% ያህል ነበር:: በሚከተለው ዓመት የማዘጋጃ ቤት ምርጫ ሲደረግ የሶሊዳሪቲ ተከታዮች ከህዝቡ ድምጽ 70% ያህል አገኙ:: ከዚያ በኋላ ግን የህዝቡ ተሳትፎ እየቀነሰ መጣ:: በ1991 ዓ.ም. በተካሄደው ምርጫ ይህ ተሳትፎ አሽቆለቆለ::

በዚህ መልክ የህዝቡ ተሳትፎ እየቀነሰ መሄዱ የሚያስደንቅ አይደለም:: ለውጦች ህዝቡ በጠበቀው ፍጥነት አይካሄዱም በመአከላዊ መንግሥትም ሆነ በአካባቢዎች ደረጃ ቦታ ቦታ የያዙት እነዚያው የቀድሞው ሥርዓት ሰዎች መሆናቸውን ተገነዘበ::ይህም የሆነበት ምክንያት ተቃዋሚ የነበሩት ኃይሎች የአስተዳደርን ሃላፊነት ለመሸከም የተዘጋጁ ሰዎች ስላልነበሩአቸው ነው::

እኔ እራሴ የዋርሶ ማዘጋጃ ቤት የመማክርት ሸንጎ አባል ነኝ:: ከዚህ ሸንጎ አባላት 80% የሶሊዳሪቲ ተከታዮች ናቸው:: ግን ከበታቻቸው ያለው አስተዳደር ያው የድሮው ነው:: የቀየርነው በቀድሞው ሥርዓት ሥር በስልጣን እጅግ በመባለግ የታወቁትን ግለሰቦች ብቻ ነው::

የአካባቢ አስተዳደርን በሚመለከት የወጣው አዋጅ ለነዚህ አስተዳደሮች በቂ የገንዘብ አቅም አይሰጣቸውም።ብዙ ገጽታዎችን ሲጥንባቸው ለዚህ መጣጣኝ የሆኑ መብቶች አልሰጣቸውም:: ስለሆነም የከንቲባው ውሳኔዎች ከሥራ ላይ የመዋል ችግር አለባቸው። ቢሮረ አስተዳደሩን ዲሞክራሲያዊ ሂደት የሚጻረሩ ብዙ እንቅፋቶች አሉ:: የህዝብ ተመራጮች የሚወስኗቸው ውሳኔዎች በፍጥነት ከሥራ ላይ አይውሉም:: እንደዚህም በመሆኑ ምንም አርኪ ለውጥ የማያየው ህዝብ በምርጫ የመሳተፉ ጥቅም አልታየው አለ:: ህዝቡ ብቻ ሳይሆን ተመራጮችም በዚህ ሁኔታ ማጉረምረም ጀምረዋል::

ዋናው ስህተት የአስተዳደሩን ተቋም አለመለወጣችን ነው ብዬ አምናለሁ:: እርግጥ ነው ያለፈው ሥርዓት ሰዎች አሁንም አስተዋጽኦ ማድረግ ይችላሉ:: ግን በደንብ እንዲሠሩ ከተፈለገ የሚሠሩባቸው ተቋሞችና መመሪያዎች መቀየር አለባቸው::

ፖሊስን በሚመለከት ሰው ሁሉ ከፍተኛ ለውጥ እንዲደረግለት ምኞት ነበረው:: በመሆኑም በጣም ብዙ ፖሊሶች ተባረሩ ግን ደግሞ ዛሬ ያለው ሁኔታ አጥጋቢ አይደለም:: የተደረገው ለውጥ የፖሊሱን ተቋም ከማናጋት በላይ በተባረሩት ፖሊሶች ቦታ ችሎታ የሌላቸው ሰዎች ተተኩ::

የካቢኔት አገዛዝ የተወሰነም ቢሆን የተረጋጋ ሁኔታ ፈጥሮ ነበር አሁን ወደ ዲሞክራሲ የሚደረገው ጉዞ ለውጥን ብቻ ሳይሆን ከለውጥ ጋር የሚመጡ ችግሮችንም ይዞ መጣ ቀደም ሲል በሥልጣን የመባለግ ክስተት እስከ ተወሰነ ደረጃም ቢሆን በካቢኔት ፓርቲው ይገታ ነበር:: አሁን ግን ሁኔታው ተቀይሯል:: በሥልጣን እየባለጉ አንዳንዶች በአጭር ጊዜ ውስጥ ይህ ነው የማይባል ሀብት በማካበት ላይ ናቸው::

4. አልጀሪያ፡

አቶ ቡህራቀ — የባእድ ሠራተኞች የጤናና ማህበራዊ አገልግሎት መ/ቤት
ቪትሪ ፈረንሳይ

አልጀሪያ ነጻ ስትወጣ የተገነባው አስተዳደር ከቀድሞው አስተዳደር የፈለቀ አልነበረም:: ብሄራዊ ነጻነታችንን ስንጎናጸፍ በዝቅተኛ ደረጃ ተነስተን አዲስና ዘመናዊ አስተዳደር መገንባት ነበረብን::

አልጀሪያ በቅኝ ግዛት በተያዘችባቸው ዓመታት በቀደመ ቅኝ ግዛት ዘመን ህብረተሰቡ ይተዳደርባቸው የነበሩት ተቋሞችም ሆነ ልምዶች እንዳልነበረ ሆነው ተደመሰሱ::

በ1962 ዓ.ም. ሃገሪቷ ነጻ ስትወጣ መሃይምነት የነገሰባት አገር ነበረች:: ከወንዶች 85% ከሴቶች ደግሞ 95% ማንበብና መጻፍ አይችሉም ነበር:: ትምህርት ከቀሰሙት ውስጥ አንዳንዶቹ ፈረንሳይኛም እንግሊዝኛም መጻፍና ማንበብ የሚችሉ ነበሩ::ግን ደግሞ አረብኛ "እንደባእድ ቋንቋ" ይወሰድ ስለነበር በዚህ ቋንቋ የተማሩ ዜጎች ትንሽ ነበሩ::

በ1962 ዓ.ም. መጀመሪያ ላይ የተኩስ አቁም ስምምነት ሲደረስ የፈረንሳይ መንግሥትና የአልጀሪያ አብዮት ተወካዮች የሚሳተፉበት ጊዜያዊ አስተዳደር ተቋቋመ:: ይህንን አስተዳደር የሚመራው ሁለቱም ወገኖች የተስማሙበት አልጀሪያዊ ነበር::

ይህ ጊዜያዊ አስተዳደር በሃገሪቱ በተለይ ጸጥታ እንዲከበር የሚያስመሰግን ተግባር ፈጽሟል ማለት ይቻላል:: በተለይ ደግሞ የሁለቱ ተዋጊ ሠራዊቶች መሪዎች ትብብራቸውን ስላለነፈጉት ይህ የአስተዳደር ሽግግር ዘመን አጥጋቢ በሆነ ሁኔታ መከናወን ቻለ::

ነጻነት ሲታወጅ አልጀሪያ ያሏት በጣም የተወሰኑ አስተዳዳሪዎች ነበር:: በመሆኑም የፖለቲካ ፓርቲያች የሙያ ማህበራት ካድሬዎች አስተዳዳሪዎች ለመሆን ተገደዱ:: ያሉት የተማሩ ዜጎች ባጭር ጊዜ ውስጥ ከፍተኛ እድገት እያገኙ ተሾሙ:: ይህም ሆኖ "ተማሩ" የሚባሉት ሰዎች የነበራቸው እውቀት አጥጋቢ አልነበረም:: በተለይ ከዩኒቨርስቲ የተመረቁ ምሁራን እጅግ የተወሰኑ ነበሩ:: በነጻነቱ ተጋድሎ ዘመን በውጭ አገር እንዲማሩ የተደረጉት ወጣቶች ገና በሚገባ ተግባራቸውን ለመፈጸም የሚችሉበት ደረጃ ላይ አልደረሱም ነበር::

ከፈረንሳይ ጋር በተደረገው የቴክኒክ ተራድኦ ስምምነት መሠረት ይህንን ችግር ለመወጣት ጥረት ተደረገ:: በዚህ ላይ ደግሞ በዓለም አቀፍ ደረጃ የአልጀሪያ አብዮት ብዙ ድጋፍ ስለነበረው ከሌሎች የውጭ ኃይሎች ድጋፍ አገኘን::

በነዚህ በመጀመሪያዎቹ የነጻነት ዓመታት የነበረብን ችግሮች እስከ አሁን ይሰማናል:: እርግጥ ነው ከፍተኛ አስተዳዳሪዎችን በማሰልጠን ብዙ ጥረት ተደርጓል:: ግን በተለይ በመሃከለኛው የእዝና የአስተዳደር ሰንሰለት ተሰማርተው ሊሠሩ የሚችሉ ብዙ የሰለጠኑ ሰዎች ማፍራት አልተቻለም::

በመጀመሪያዎቹ አሥር ዓመታት ውስጥ ይህን ችግር ለመወጣት በሃገሪቱ በራሷ ጥረት፣ እንደዚሁም በውጭ እርዳታ አማካኝነት ብዙ ተሞከረ:: መሀይምነትን ለማጥፋት ከፍተኛ ዘመቻ ተካሄደ:: የትምህርት መስፋፋትና የመንግሥት አስተዳደር ዘመናዊ መሆን ተያይዘው አብረው ያደጉ ክስተቶች ናቸው::

የትምህርት ደረጃ ቀስ በቀስ እያደገ ሲሄድ የከፍተኛ ትምህርት ተቋሞችም በዚያው ልክ እያደጉ መጡ:: አልጀሪያ የራሷን ምሁራንና አስተዳዳሪዎች ማፍራት ጀመረች:: ከነጻነት በፊት ዩኒቨርስቲ ተማሪ የነበሩት የአልጀሪያ ዜጎች በደርዘን ብቻ የሚቆጠሩ ነበሩ::በሺህ መቁጠር ጀመሩ:: ከ10ኛው ዓመት በኋላ በተከተለው ወቅት ደግሞ በደርዘን ሺህ መቁጠር ጀመሩ::

ይህም ሆና ለወዝደሮች አስፈላጊ የሆነው የሙያ ትምህርት በተመጣጣኝ ሁኔታ እድገት አላሳየም:: ይህ ጉድለት ዛሬ ትልቅ እንቅፋት እየሆነ ሰመጣ ይታያል:: በዚህም የተነሳ የሀገሪቱ የኢኮኖሚ እድገት መሪያቿም ህዝቧም ከሚጠብቀው እኩል መራመድ አልቻለም::

አልጀሪያን ከለሙት አገሮች ደረጃ ለማድረስ ብዙ ጥረት ተደርጓል ግን ደግሞ ወጭ ከተደረገው ከፍተኛ ገንዘብ አንጻር ሲታይ ለሰዎች በልጽግና ለማስገኘት የተደረገው ጥረት አጥጋቢ እንዳልሆነ ግልጽ ነው:: ቀደም ሲል አመቺ የነበረው የአለም አቀፍ ኢኮኖሚ ሁኔታ ቀውስ ውስጥ ሲገባ በአልጀሪያ የነበረው ይህ መሠረታዊ ድክመት እየተገለጠ መጥቶ ሃገሪቱን ወደ ሌላ ቀውስ አስገባት::